# ክፍለ ትምህርት ሁለት

# መሪዎች ሰዎችን ያደንቃሉ

በአንደኛው ክፍለ ትምህርት ላይ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የመሪነት ቦታ እንዴት እንደሆነ በመግለጽ፣ በመሪነት ስፍራ ላይ ሆነው የተሳካላቸውን ሰዎች ባሕርያት በመዘርዘር ተመልክተናል። ከዚያም ከመጽሐፍ ቅዱስ የዮሴፍን ምሳሌነት በመውሰድ ለመንፈሳዊ መሪነት ስለተሰጡ መስፈርቶችና ኃላፊነቶች በመጠኑ በመዳሰስ ተገቢውን ግንዛቤ ለማግኘት ችለናል።

በዚህ በሁለተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የምንመለከተው የሙሴን ምሳሌነት በመከተል አንድ መንፈሳዊ መሪ ከሌሎች ጋር ሊኖረው የሚገባው ግንኙነት እንዴት መሆን እንዳለበትና አብረውት ለሚሠሩ ሰዎች የሚኖረው አስተያየት ምን መሆን እንዳለበትና የመሪነትን ዘዴ እንዴት ማዳበር እንደሚችል እንመለከታለን።

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የሙሴ ምሳሌነት
- መሪዎች ስለ ሰዎች ምን እንደሚያምኑ
- የመሪነት ዘዴ እንዴት ማዳበር እንደሚቻል

---

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የሙሴን ሕይወት መሠረት በማድረግ የመሪነትን መመሪያዎች መግለጽና እነዚህ መመሪያዎች በተግባር የሚተረጎሙበትን መንገድ ለይቶ ማወቅ።

- አንድ መሪ አብረውት ከሚሠሩት ሰዎች ጋር ያለው እምነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ።
- የመንፈሳዊ መሪነትን መመሪያዎች አስመልክቶ የተለያዩ የመሪነት ዘዴዎችንና ባሕርያትን መገምገም።

-----------------------------------------------------------------------

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1/ በትምህርት 1 ላይ እንዳደረግኸው ሁሉ የክፍለ ትምህርቱን ዓላማዎች አንብብ።
2/ ከዘጸ 2-7፣11-18፣ 35-36 የሙሴን ታሪክ አንብብ። በዚህ ትምህርት የምንጠቀምባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ የምንባብ ክፍሎች ዘጸ 2-3፣ 4፡1-17፣31-34፣10-31፣15፡22-25፣16፣1-11፣17፣1-15፣19፣9-26፣ 32፣1-14፣ 35፣1-36፣1-7 ላይ የሰፈሩት ናቸው።
3/ ክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ በጥንቃቄ ካጠናህ በኋላ በቅደም ተከተል የሰፈሩትን ጥያቄዎች መልስ:: ከዚያም በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት ጋር በማስተያየት ትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

## የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ- የሙሴ ምሳሌነት

### ዓላማ 1 ሙሴ ለመሪነት እንዴት እንደተጠራና የሰጠውን ምላሽ ለመግለጽ

የሙሴ ሕይወት ታሪክ የመሪነት ታሪክ በመሆኑ፣ ስለ መሪነት ከተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ እግዚአብሔር ከመሪዎች ጋር፣ መሪዎች ደግሞ ከሰዎች ጋር ያላቸውን የቅርብ ግንኙነት ለማጥናት የእርሱን ያህል የሚረዳ የለም።

እንደብዙዎቹ የጌታ አገልጋዮች ሙሴም ስለ ሰዎች መቆርቆር የጀመረው ገና ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ ነበር። ሰዎች ያሉበት ሁኔታ ያሳስበዋል፣ እነርሱን ለመርዳት አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበትም ያስባል። በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ግልፍተኝነት ያለበት ነበር። ከእግዚአብሔር ምሪት አለመጠየቁም እውነት ነው።

የፍትሕ መዛባትን በራሱ ጥረት ለማስወገድ ነበር የፈለገው። ይህም ሙከራው ሰው እንዲገድል አድርጎታል ዘጸ 2፡11-15።  አገር ጥሎ በኮበለለበት ጊዜ እንኳ ይህ ፍትሕ የማስከበርና ለሰዎች የመቆርቆር ስሜቱ አብሮት ነበር። ይህንንም ለመገንዘብ የምንችለው በዘጸ 2፣16-19 ላይ ውኃ ለመቅዳት መጥተው የነበሩትን ልጃገረዶች እረኞች ባጉላሉዋቸው ጊዜ ካሳየው ተቆርቋሪነት ነው። ይህም መልካም ሥራው ከዮቶር ጋር ስለአቀራረበው ልጁን ለማግባት በቃ። አንድ ቀን የአማቹን በጎች በመጠበቅ ላይ እያለ ቁጥቋጦው በሚያስገርም ሁኔታ ሲነድ አየውና፣ በቅርብ ለመመልከት ተጠጋ። ሙሴ የተረጋጋና የሁኔታዎችን ምንነት ለማወቅ የሚፈልግ፣ ያልተለመዱ ክስተቶችንም ቀረብ ብሎ መረዳት የሚወድ ሰው ነበር።

ከሚነድደው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር *"ሙሴ፣ ሙሴ"* በማለት ጠራው። ሙሴም እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመስማት ዝግጁ ሆኖ *"እነሆኝ"* በማለት መልስ ሰጠ። እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥለት ግን በአክብሮታዊ ፍርሐት ፊቱን ሸፈነ። ጌታም ***"የሕዝቤን መከራ አይቼአለሁ፣ መከራቸውንም ተመልክቼአለሁ፣ ስለዚህም ከዚያ ምድር ላወጣቸው መጥቻለሁ። ሕዝቤን ከግብጽ እንድታወጣ ወደ ፈርዖን እልክሀለሁና ሂድ"*** አለው።

ከዚህ ላይ እንደገና የምንመለከተው የእግዚአብሔርን የአሠራር ዘዴ ነው።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ዓላማ ስላለው፣ ዓላማውን ለመፈጸም መሪ መረጠ። በዚህ ጊዜ ግን ሙሴ እንደበፊቱ ግልፍተኛ አልነበረም፣፡ የራሱን ደካማነት መረዳት ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ዓላማ ካሰበውና ከጠበቀው በላይ እንደሆነ ተገነዘበ። እንዲህ ያለውን ትልቅ ዓላማ የከብቶች እረኛ የሆነ እንደ እርሱ ዓይነት ሰው ሊወጣው የሚችል መስሎ ስላልታየው፡- ***"ይህን ለማድረግ እኔ ማነኝ? አንተ እንደላክኸኝስ እንዴት አስረዳቸዋለሁ"?*** በማለት ጠየቀ።

አንድ መሪ ሙሉ ሥልጣን ሊኖረው እንደሚገባ ሙሴ ተረዳ። ጌታም በድንቆችና በተአምራት መልክ ሥልጣንን እንደሚሰጠውና አብሮት እንደሚሆን እንደዚሁም በሥራው እንደሚረዳው ለሙሴ ቃል ገባለት። የነገረው ዓላማውን ለመፈጸም

እንዲችል እንደሚረዳው እንጂ ለግል ክብሩ ሽልማት እንደሚያገኝ አልነበረም። ይህም ሁሉ ሆኖ ሙሴ ያለው በማመንታት ላይ ነው።

*"አጥርቼ መናገር አልችልም፣ እባክህን ሌላ ሰው ላክ"* አለ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጣ። ትሕትና መልካም ነው። ትሕትና ግን በእግዚአብሔር ካለን እምነት ጋር መመጣጠን አለበት። እግዚአብሔር ተስፋውን እንደሚፈጽም ልንታመንበት ይገባል። አሮን በእርሱ ምትክ ሆኖ እንደሚናገርለት እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው። ሙሴና አሮን የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሰበሰቡና የእግዚአብሔርን እቅድ ይነግሩዋቸዋል። ይህን በመሰለ ሁኔታ እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያዎችን እንደሰጠው እያንዳንዱ መሪ ኃላፊነቱን ይረዳል፣ ይቀበላል። አሁን ሙሴ ሙሉ በሙሉ ራሱን ለእግዚአብሔር ሰጥቷል:: መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ *"ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ"* ይላል።

1/ ከፊት ለፊት ያለውን ፊደል በመክበብ እውነተኛ የሆነውን መግለጫ አመልክት።

ሀ/ የእግዚአብሔርን ጥሪ እስከሰማበት ሙሴ ለሕዝቡ ደንታ አልነበረውም።

ለ/ እግዚአብሔር ለሙሴ የመሪነት ሥራን ከመስጠቱ በፊት እንኳ ለህዝቡ ያስብ እንደነበር ገልጧል።

መ/ ትሕትናና በእግዚአብሔር መታመን ለአንድ መሪ አስፈላጊ እንደሆነ ከሙሴ ልምምድ መገንዘብ እንችላለን።

ሠ/ የሙሴ መሪነት በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ የተመሠረተ ነበር።

ረ/ ታላቅ ኃላፊነት እንደተቀበለ ሙሴ ተረድቷል።

**እነዚህን ሰዎች ምን ላድርጋቸው?**

**ዓላማ 2 ዮቶር ለሙሴ ከሰጠው ትምህርት ከሰዎች ጋር ለመሥራት አራት መንገዶችን ለመጥቀስና ተግባራዊ የምናደርግባቸውን መንገድ ለማሳየት**

የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ምሪት በመቀበሉ ሙሴ የእሥራኤልን ሽማግሌዎችንና ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት እንዲወጡ አዘጋጃቸው። የፈርዖን ልብ ደነደነ። እግዚአብሔርም

በምድሩ ላይ መቅሰፍት አወረደ፡፡ በመጨረሻም ፈርዖን ሕዝቡ ከግብጽ እንዲወጡ ፈቀደ ዘጸ 12፣31፡፡

ሴቶችና ሕጻናትን እንዲሁም የቤት እንስሳትን ጨምሮ /ስድስት መቶ ሺህ/ ወንዶች ሰዎችን መምራት ምን ያህል ከባድና አስቸጋሪ እንደሆነ መገመት አያዳግትም/ዘዳ 12፣37/፡፡ በአገር አቀፍ ወንጌል ዘመቻ ስብሰባ በማዘጋጀት ተሳትፈህ የምታውቅ ከሆነ ያንን ያህል ሕዝብ መምራት ለሙሴና ለረዳት መሪዎቹ ምን ያህል ከባድ ሊሆንባቸው እንደሚችል በቀላሉ መረዳት ትችላለህ፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ሕዝቡ በስሜት በመንቀሳቀሳቸው እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ማንቀሳቀሱ ከባድ አልሆነም፡፡ አንድ አዲስ እንቅስቃሴ ሲጀመር ሰዎች ያለምንም ጥያቄ መሪዎቻቸውን መከተላቸው የተለመደ ሰብአዊ ባሕርይ ነው፡፡ ትንሽ ቆይተው ግን ችግሮች ሲገጥሙአቸው ስሜታቸው እየቀዘቀዘ ሲሄድ አንዳንድ ጥያቄዎችን ማንሣት ይጀምራሉ፡፡ ማጉረምረም ይጀምራሉ፡፣ ከዚያም አልፈው በመሪያቸው ላይ በጠላትነት ይነሳሉ፡፡ በሙሴ ላይ የደረሰውም ይኸው ነበር፡፡

2/ ዘጸ 14፣10-12፣15፣23-25፣ 16፣2-3፣ 17፣1-3 አንብብ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች በእሥራኤላውያን ጉዞ ወቅት ከተፈጸሙ አራት ድርጊቶች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ሁኔታ ሕዝቡ ምን አደረጉ? መልስህን በተሰጠው ሰፍራ ላይ አስፍር፡፡

በመጨረሻም ውሀ የሌለበት ሥፍራ ሲደርሱ ሕዝቡ አጉረመረሙ፡፡ ሙሴም **"ይኸን ሕዝብ ምን ላድርገው"?** ብሎ ወደ ጌታ ጮኸ፡፡ እንደ ሌላው ጊዜ ሁሉ አሁንም እግዚአብሔር የሕዝቡን ችግር ለማቃለል ተአምር አደረገ፡፡ እዚህ ላይ ግን እግዚአብሐር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ከሕዝብ ጋር እንደሚሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ተጨማሪ የአሠራር ዘዴን ያሳየናል፡፡

3/ ዘጸ 17፣5 አንብብ፡፡ ሙሴ ከእግዚአብሔር ሦስት መመሪዎች ተቀበለ ፡፡ ከሕዝቡ ፊት ለፊት መሄድ፣ በትሩን መያዝና ሦስተኛው መመሪያ ምንድነው?

በእሥራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ ፊት ሙሴ አለቱን በበትር መታው። ከዐለቱም ውሃ ወጥቶ ሕዝቡ ሁሉ ጠጡ። ለዚህ ሽማግሌዎቹ ምስክር ናቸው። የሙሴን አገልግሎት ልምምድ በቅርቡ የሚካፈሉበት ሁኔታ ተፈጠረላቸው። እርሱ ሲማሩና ለአገልግሎታቸውም አዲስ እምነትና ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል። መሪዎች የአገልግሎት ልምምዳቸውን ለሕዝቡ ያካፍሉ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ ያሳየናል። በአዲስ ኪዳንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌዎቻችን ናቸው።

በሚቀጥለው ሁኔታ ደግም በመሪዎችና በተመሪዎች መካከል ስለነበረው ቅርርቦሽ ምሳሌያዊ ገለጻ እናያለን። ሙሴ ኢያሱን መረጠ። ኢያሱ ደግሞ ከእስራኤል ጠላቶች ጋር የሚዋጉ ሌሎች ሰዎችን መረጠ። በጦርነቱ ጊዜ ሙሴ እጆቹን ለጸሎት ወደ እግዚአብሐር አንሥቶ ነበር። እጆቹ ዝለው ሲያወርዳቸው ጠላት ያሸንፋል። ስለዚህም ሙሴ ቁጭ አለና ሌሎች ግራና ቀኝ ሆነው እጆቹን እንዲደግፉ በማድረግ በዚህ ሁኔታ ጦርነቱ በድል ተጠናቀቀ። እግዚአብሔርም ሙሴን፣ ***"ይህን ለመታሰቢያ ጻፈው"*** አለው ዘጸ 17፣14። የአንድን መሪ እጆች እንዳይዝሉ የሌሎች መሪዎች ድጋፍ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

እንደ ማንኛውም መልካም መሪ ሁሉ የሙሴም ፍላጎት ዓላማውን እግቡ ለማድረስ ነበር። ለሥራው ራሱን የሰጠና ትጉህ መሪ በመሆኑ ሥራው እንዲሳካለት የሌሎች ትብብር ያስፈልገዋል። እርሱ ራሱን በሰጠበት ሁኔታ ሰዎች ለሥራው ራሳቸውን አለመስጠታቸውን ሲያይ ደግሞ ያዝናል። ሕይወቱን ለመስጠት እንኳ ፈቃደኛ እስኪሆን ድረስ ሕዝቡን ይወዳል። ይሁን እንጂ መሪነትን የሚመለከት ሌላ ዓይነት ፍቅር መማር ነበረበት። ይህ ዓይነት ፍቅር ደካማ ሆነው ቢገኙ እንኳ በሰዎች መታመንን፣ ራዕያቸውን መካፈልንና ለግቡ መሳካትም አስፈላጊውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማበረታታትን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሙሴ ይህን የተማረው ከአማቹ ከዮቶር ነበር።

ዮቶር ወደ ሙሴ ሲመጣ እግዚአብሔር ያደረገውን ድንቅ ነገርና ስለ ጉዞአቸው ተወያዩ። ምናልባትም ስለ ሕዝቡ ማጉረምረምና እግዚአብሔርንና እርሱን እንዳሳዘኑ

ሳያጫውተው አልቀረም፡፡ ምናልባትም ለጌታ እንደተናገረው ሁሉ **"ይኸን ሕዝብ ምን ላድርገው?"** በማለት ሳይጠይቀው አልቀረም፡፡

ሙሴ ከሕዝቡ ጋር የነበረውን ቅርበት ዮቶር በየዕለቱ ይመለከት ነበር፡፡ ምን ያህል ሙሉ በሙሉ ለጌታ ሥራ ሕይወቱን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን እንደሰጠ አይቷል፡፡ ሰዎች በየዕለቱ ወደሙሴ ይመጣሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው እንደዳኛም፣ እንደአማካሪም፣ እንደአገልጋይና ረዳት ሆኖ ነበር ሕዝቡን የሚመራው፡፡ **"ሥራው ከባድ ስለሆነ ብቻህን አትችለውም፣ ስለዚህ ከሰማኸኝ ምክር ልስጥህ"** አለ ዮቶር፡፡ እንደገና ዘጸአት 18፣13-26 አንብብ፡፡ ከዚህ ዮቶር ለሙሴ ከሰጠው ምክር ከሰዎች ጋር ስለ መሥራት አራት ነገሮችን ትመለከታለህ፡፡

1/ ሕግና ደንብ አስተምራቸው፡፡

2/ እያንዳንዱን ሥራ እንዴት እንደሚሠሩ አሳያቸው

3/ ለየግላቸው የተለየ ሥራ ስጣቸው

4/ መካከለኛ መሪዎችን ምረጥና ሥራውን አብረሀቸው አደራጅ፡፡

ሙሴ ላቀረበለት ጥያቄ ዮቶር የመለሰለት እነዚህን ነበር፡፡ ሙሴ እነዚህን ምክሮች ከተቀበለ በመጀመሪያ ደረጃ የሥራ ጫና ይቃለልለታል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሕዝቡም በሥራው ይረካሉ፡፡ እነዚህን ሁለት ነጥቦች ዘወትር ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡ የተዋጣለት የአመራር ዘዴ እነዚህን እንደሚያጠቃልል በኋላ እንመለከታለን፡፡ ዓላማን እግቡ ማድረስና የሠራተኞችም ፍላጎት ሊሟላ የሚቻለው እነዚህ ሁለት ነጥቦች በሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ነው፡፡

4/ ከሰዎች ጋር ስለመሥራት ዮቶር ለሙሴ የሰጣቸውን አራት ነጥቦች እንደገና አንብብ፡፡ መጽሐፉን እጠፍና በአእምሮህ የያዝካቸውን ጻፍ፡፡ ይህ እያንዳንዱ መንፈሳዊ መሪ ሊከተለው የሚገባ መልካም ምክር ነው፡፡

5/ ዘጸ 18፣22 አንብብ፡፡ በ17፣5 ላይ ከተመለከትነው የመሪነት አሰራር ጋር ተመሳሳይ የሆነ የመሪነት መመሪያ የያዘ መሆኑን ልብ ብለህ አስተውል፡ ያም የሙሴ የሥራ ጫና መቃለል የነበረበት ስለሆነ ነው፡፡

**የእግዚአብሔር ሕዝብና የሙሴ ሕዝብ**

## ዓላማ 3 ምንም እንኳ በአንዳንድ ሁኔታ ቢያሳዝኑትም ሙሴ ከሕዝቡ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ እንደነበር ለመግለጽ

ሙሴን ታላቅ መሪ ካደረጉት ነገሮች አንዱ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማየት መቻሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስሙን ለማክበርና ዓላማውንም ለመፈጸም በሰዎች አማካይነት እንደሚሠራ ያውቃል፡፡ በቃልም ሆነ በድርጊት ሙሴ እግዚአብሔር ከሰጠው ሕዝብ ጋር አብሮ ለመሥራት የነበረውን ፈቃደኝነት ያሳያል፡፡ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ፣ ለእግዚአብሔር ለመሥራትም ያለው ዓላማ ሰዎችን እንዲወድና ታማኝ እንዲሆንላቸው ረድቶታል፡፡

በዘጸ 18፣15 ላይ ለምን ጊዜውን በብዛት ከሕዝቡ ጋር እንደሚያሳልፍ ዮቶር በጠየቀው ጊዜ ሙሴ የሰጠው መልስ ምን ነበር? **"ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ወደ እኔ ስለሚመጡ ነው"** ነበር ያለው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሕዝቡ አልፎ አልፎ ቢያምጹም፣ ሙሴንም ያለአግባብ ቢወቅሱትም፣ በጌታ ባይታመኑም፣ በልባቸው እግዚአብሔርን ለማወቅና እርሱንም የማገልገል ፍላጎት እንደነበራቸው ነው፡፡ ለመማር ይፈልጋሉ፡፡ ችግር ሲደርስባቸውም ምክርና እርዳታ ፍለጋ ነበር ወደ ሙሴ ይመጡ የነበሩት፡፡ ከሰዎች ጋር ለሚኖራቸው አለመግባባት የጌታን ውሳኔ እንደመጨረሻው መፍትሄ አድርገው ነበር የሚቀበሉት፡፡ የእሥራኤልን ጠላት በጀግንነት ተዋግተዋል፡፡ የተለያየ ድካም ቢኖርባቸውም ሙሴ እነዚህን መልካምና ጠንካራ ጎኖቻቸውን አስተውሏል፡፡

በዘጸአት ምዕ 32 ላይ እንደምናነበው ሙሴ በሲና ተራራ ላይ የእግዚአብሔር ቃል በሚቀበልበት ወቅት ሕዝቡ የወርቅ ጥጃ ምስል ሠርቶ በባእድ አምልኮ ኃጢአት ውስጥ በወደቀ ጊዜ ሙሴ ከተራራው ሲመለስ ይህን ተመልክቶ ልቡ በሐዘንና በብስጭት እንደተሰበረ ከፈጸመው ድርጊት በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ከቁጥር 7-14 ላይ የተጻፈው በእግዚአብሔርና በሙሴ መካከል የተደረገ ንግግር ዘወትር ልናስታውሰው የሚገባ ነው፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን *“ከግብጽ ምድር ያወጣኸው ሕዝብህ ኃጢአት አድርጓል- አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ፣ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሀለሁ”* አለው ሙሴ ግን *“አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ለምን ተቃጠለ? ከመዓትህ ተመለስ፣ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ”* ሕዝቡ ደካሞች ስለሆኑ ኃጢአት አደረጉ። ይበልጥ ትምህርትና ምሪት አስፈለጋቸው፣ ያም ሆኖ የእግዚአብሔር ሕዝብና የሙሴ ሕዝብ ነበር።እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሙሴን ኃላፊ ሲያደርገው ሙሴም በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ኃላፊነቱን ተቀብሎ በእግዚአብሔር እርዳታ በትክክለኛው መንገድ ሲመራቸው ሙሴ ሕይወቱን ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ሰጠ። በባዕድ አምልኮ ምክንያት ከደረሰባቸው ውድቀትና ጥፋት በኋላ እንደገና አደራጃቸው። ችሎታቸውን ስጦታቸውን ተጠቅመው የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠሩ ያነሳሳቸውም እርሱ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል አስተማራቸው። የሚሠሩትን ሥራ ካሳያቸው በኋላ እርሱ ጀምሮት በነበረውን ሥራ እነርሱ እንዲፈጽሙ ተወላቸው።

7/ የሚከተለውን ዓረፍተ ነገር ይበልጥ የተሟላ በሚያደርገው ፊደል በማክበብ አመልክት። ምንም እንኳ አልፎ አልፎ ቢያሳዝኑትም ሙሴ ከሕዝቡ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነበት ምክንያቱም፡-

ሀ/ ያን የሚያህል ሕዝብ መምራት ክብር ስለሆነ

ለ/ ማደግና መዳበር የሚችል ብርታት እንደነበራቸው ስላስተዋለ

ሐ/ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸም ያላቸውን ፍላጎት ስላየ

መ/ በእነርሱ አማካይነት እግዚአብሔር እንዲከብር ስለፈለገ

ሠ/ የመሪነት ችሎታውን ማሳየት ስለፈለገ

**መሪዎች ስለ ሰዎች ምን እንደሚያምኑ**

**ዓላማ 4 ዮቶር ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የነበረውን ግንዛቤ ለመግለጽ**

ዮቶር ለሙሴ የሰጠውን መልካም ምክር ከሰዎች ጋር አብሮ ለመሥራት የማያስችል ከመሆኑም በላይ፣ አጠር ባለ መልኩ ስንመለከተው ከተከታዮቹ የበለጠ መልካም ነገርን እንዲጠብቅ የሚያደርግ ምክር ነበር፡፡

አንዳንድ ስለ መሪነት ጥናት ያደረጉ ምሁራን አንድ መሪ የሚወስደው እርምጃ በሕዝቡ ላይ ያለው እምነት ውጤት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እንደእነዚህ ምሁራን አባባል ለሰዎች ያሉን እምነቶችና ግምቶች ይባላሉ፡፡ ከሰዎች የምንጠብቀው ነገርና ስለ እርሱም ያለን አመለካከት እንደዚሁም የምንወሰደው እርምጃ በእነዚህ ግምቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ወጣቶች በእድሜ ከገፉት ሰዎች ይልቅ ይበለጥ ጠንካሮች ናቸው የሚል ግምት ሊኖረን ይችላል፡፡ ስለዚህም አንድ የምናንቀሳቅሰው ከባድ ነገር ቢኖር ከባድ የሆነውን ሥራ ወጣቶች እንዲሠሩት እናደርጋለን፡፡ ይህን ቢኖር ከባድ የሆነውን ሥራ ወጣቶች እንደሚቀበሉም ተስፋ እናደርጋለን፡፡ አንድ ሰባኪ የሚናገረው ነገር ስለ ምዕመኑ ያለውን እምነት እንዴት እንደሚያሳይ እንመልከት፡፡ ለምሳሌ ያህል ምዕመኑን “ለግል ጉዳያችሁ ከምታባክኑት ሰፊ ጊዜ ውስጥ ጥቂቱን ነፍሳትን ወደጌታ ለማምጣት ልታውሉት ይገባል” ቢላቸው ይህ ሰባኪ የሚያሳየው ምን ግምቶች ነው?

ሰባኪው ለሕዝቡ ያለው ግምት፡-

1/ ሰዎች ጊዜያቸውን የሚያባክኑት ለደስታ ብቻ እንደሆነ

2/ በጊዜ አጠቃቅም ራስ ወዳዶች እንደሆኑ

3/ መሥዋዕትን ስለሚጠይቅ ጊዜያቸውን ነፍሳትን ወደጌታ ለማምጣት እንደማይፈልጉ

4/ ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ ነፍሳትን ወደ ጌታ ያመጡ እንደነበር

በሰባኪው ግምት ሕዝቡ ደስታን ስለሚወድ ነፍሳትን ወደ ጌታ ለማምጣት ደንታ የላቸውም፣ ስለዚህም ለነርሱ ያለው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ነፍሳትን ወደ ጌታ እንዴት ማምጣት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይፈልጋል፡፡ የሚያስፈለገውን መስዋዕትነት ቢከፍሉ ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት እንደሚችሉ እምነት አለው ማለት ነው፡፡

ስለሆነም፡- እንዴት ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት እንደሚችሉ ትምህርት እንደሚሰጥ ይነግራቸዋል እንበል፡፡ ስለዚህም ”ላልዳኑ ሰዎች የምስራቹን ቃል

ስለማካፈል በይበልጥ መማር ትችላላችሁ” ቢላቸው ግምቶቹ በይበልጥ ይህን ይመስላሉ፡-

1/ ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት ደስ ያሰኛቸዋል፣ እንዴት እንደሚያመጡ ግን አያውቁም፡፡ ስለዚህ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡

2/ ጊዜያቸውን በሥልጠናውና ነፍሳትን ወደጌታ ለማምጣት ቢያውሉት ፈቃደኛ ናቸው፡፡

3/ ስላልዳኑ ሰዎች ያስባሉ

እንግዲህ ከዚህ እንደምንመለከተው ሰባኪው ለሕዝቡ ከፍተኛ ግምት አለው፣ ይሁን እንጂ ሥልጠና ይጎድላቸዋል፡፡ ስለዚህም ያላቸውን ችሎታ ለማጎልበት እንዲጠቀሙበት ይፈልጋል፡፡

8/ የተሻለ መልስ ነው የምትለውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡

ሀ/ ያለምንም ድርጅት ሰዎች እንደሚገባ መሥራት ይችላሉ

ለ/ አብዛኞቹ ሰዎች የግል ችግራቸውን ያለ ረዳት መፍታት ይችላሉ፡

ሐ/ እንደሚገባ ካስረዷቸው ሰዎች መመሪያን ለመቀበል ዝግጁ ናቸው

ሠ/ አብዛኞቹ ሰዎች በሚያደርጉት ውሳኔ እምነት ሊኖረን ይገባል

## የአመራር ዘዴ እንዴት እንደሚዳብር

## ዓላማ 5 የመሪነትን ባሕርይ ምሳሌዎች፣ ስለ ሰዎች ከተሰጡ ግምቶች ጋር ለማዛመድ

ስለ ሰዎች ያለን ግምቶች የመሪነትን ዘዴ በማጎልበት ረገድ እንዴት ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የመጀመሪያው ጥናት እንዳቀረበው የብዙዎቹ መሪዎች ባሕርያት የተመሠረቱት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ግምቶች ላይ ነው፡፡ ግምቶቹም ሰዎች ሥራ ስለማይወዱ በተቻላቸው መጠን ከሥራ ይሸሻሉ፡፡ ይፈልጋሉ ኃላፊነትን ለማስወገድ እንጂ ለመቀበል አይፈልጉም ፡፡ ሰፊ ግቦች ላይ ለመድረስ ያላቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ዓላማዎችንና ግቦችን በአገር አቀፍ የወንጌል ማስፋፋት፣ እንቅስቃሴ መሳተፍ ድርጅታዊ ዓላማዎችንና ግቦችን የሚጠይቅ ነው፡፡

ከጥናቱ የተገኘው ከዚህ ተቃራኒ የሆነው አመለካከት ደግሞ እነዚህ ግምቶች የሚያጠቃልሉት ከዚህ የሚከተሉትን ነው። ሥራ የሰዎች ተፈጥሮአዊ ባሕርይ በመሆኑ ሊርቁት ወይም ሊያስወግዱት ዝንባሌ የላቸውም። ሰዎች ዓላማዎችን እግቡ ለማድረስ በፈቃደኛነት ይሠራሉ። ሰዎች ኃላፊነትን መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ኃላፊነትንም ይሻሉ የሚል ነው።

በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉት ጥቂቶቹ ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላው ብዙ ሰዎች ሰፋፊና ትላልቅ ግቦችን ለመምታት የግላቸው አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል። ብዙ ሰዎች ገና ሥራ ላይ ያልዋለ ችሎታና ኃይል አላቸው። ሰዎች ዋጋ ይኖራቸዋል ብለው ለሚያምኑባቸው ዓላማዎችና ግቦች ራሳቸውን ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

አሁን ደግሞ ስለ ሰዎች ያለን ግምት እንዴት የመሪነት ስልትን ወይም ዘዴን ለማዳበር እንደሚረዳን ግንዛቤ ለማግኘት ብንሞክር ስልት ወይም ዘዴ የሚለውን ቃል አስቀድመን መግለጽ ይኖርብናል። የባሕርያት ክምችት ወይም ሥራዎቻችንን የምናከናውንበት መንገድ በማለት ስልት ወይም ዘዴ የሚለውን ቃል ልንገልጸው እንችላለን። ስለ መሪነት የተጻፉ አብዛኛዎቹ መጻሕፍት ጥቂት የአመራር ስልቶችን አስፍረዋል። አብዛኞቹ ፀሐፊዎች የገለጹአቸው ሁለት ስልቶች ሲሆኑ አንደኛው ገደብ የሌለው ስልጣን ያዘለ ሲሆን፣ ሌላው ብዙሐኑ የሚሳተፉበት የአመራር ስልት ነው። ገደብ የሌለው ሥልጣን ያዘለ የአመራር ስልትን የሚከተል መሪ ብዙኀኑን ይቆጣጠራል። ውሳኔዎችን ሁሉ የሚያደርገው ራሱ ነው። ደንቦችን የሚያወጣውና ተፈጻሚም የሚያደርጋቸው እርሱ ራሱ ነው። ከበታቹ ሆነው እንዲሠሩ ዝርዝር መመሪያ ይሰጣቸዋል። በቅርበትና በግል ማንኛውንም እንቅስቅሴ ይቆጣጠራል።

ብዙኃኑን በሚያሳትፍ በአመራር ስልት የሚጠቀም ሰው በቡድኑ ውስጥ ሆኖ ነው እርሱ ራሱ የሚሠራው። ደንቦቹን እንዲያወጡ ይመራቸዋል። ውሳኔ በመስጠት እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል። የሌሎችን ምክርና አስተዋጽኦ ይጠይቃል። ለአንዳንድ የቡድኑ አባላት አንዳንድ አስፈላጊ ኃላፊነቶችን ይሰጣቸዋል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የመጀመሪያውን የጥናት ግምት የሚቀበል መሪ አብዛኞቹ ሰዎች ቸልተኛ፡ ሰነፍና ሥራ የማይወዱ እንደሆኑ ያስባል፡፡ "ግፊት" ሊሰጣቸውና ከበላይ ሆነው እንዲቆጣጠሩዋቸው ያስፈልጋል የሚል እምነት አለው፡፡ ምሪት፣ ቁጥጥር፣ መገፋፋትና ተግሳጽ ያስፈጋልጋቸዋል ይላል፡፡ ስለዚህም እንዲህ ያለ እምነት ያለው መሪ ሰዎች እሚፈለገው ግብ ላይ እንዲደርሱ ከተፈለገ ሙሉ ለሙሉ ልንቆጣጠራቸው ያስፈልጋል በማለት ያስባል፡፡ ውሎ አድሮ ፈላጭ ቆራጭ ይሆናል፡፡

ሁለተኛውን የጥናት ግምት አመለካከት የሚከተል ሰው ሰዎች ሥራ ወዳዶች እንደሆኑና እሚፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ ኃላፊነትን የመቀበል ፍላጎት እንዳላቸው ያምናል፡፡ ለዚህም አንዳንድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በችሎታቸውና በስጦታዎቻቸው በመጠቀም ተሳትፎ እንዲኖራቸውም ያደርጋል፡፡ ይህን ሁሉ የሚያደርገው ፈቃደኛነታቸውን በማክበር ነው፡፡ እንዲህ ያለው መሪ ብዙኅኑን የሚያሳትፍ መሪ ነው፡፡

9/ ገደብ ከሌለው የአመራር ስልትና ብዙሃኑን ከሚያሳትፈው የአመራር ስልት የምትከተለው የትኛው እንደሆነ ምክንያትህን ጭምር በመግለጽ መልስህን በተሰጠው ስፍራ አስፍር፡፡ ----------------------------

እርግጥ ነው፣ ሥራ የማይወዱ አንዳንድ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ይልቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡ ለዓላማው መሳካት አስፈላጊ ሆኖ እስካገኘው ድረስ መሪው ዝርዝር መመሪያዎችን መስጠት፣ ማስፈጸምና በአቋሙም የማያወላውል ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ መልካም መሪዎች እንደሰዎቹ ዓይነትም እንደ ሁኔታዎቹ ልዩነት የአሠራር ዘዴያቸውን በመለዋወጥ ይጠቀማሉ፡፡ በኂለኛው ትምሕርታችን ስለዚህ ብዙ የምናጠናው ይኖረናል፡፡

እዚህ ላይ በጣም ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን ጉዳይ ግን የአመራር ስልታችን የሰመረና የተዋጣልን መሪዎች መሆን የምንችለው ለሰዎች በሚኖረን ግምት መጠን መሆኑን ነው፡፡ ክርስቲያኖች ዋጋ እንዳለው ለሚያምኑበት ዓላማና ግብ ራሳቸውን ይሰጣሉ፡፡ ምክር ፍለጋ ወደ ሙሴ ይመጡ እንደነበሩት ሰዎች ሁሉ ክርስቲያኖችም

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈልጋሉ። የክርስቶስን አካል በመገንባቱ ሥራ ይሳተፋሉ። ከጌታ የተቀበሏቸው ስጦታና ችሎታዎች አሏቸው። በጌታ ሥራ በሚደርጉት ተሳትፎ ደስታና ክብር ይሰማቸዋል። ስለዚህም ያላቸውን ስጦታና ችሎታ እንዲያዳብሩ የሚረዳቸውን መሪ ይፈልጋሉ። በእግዚአብሔር እቅድ መሠረት የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠሩ ሲነገራቸውም ሙሴ ይህንኑ ነበር ያደረገው።

10/ ዘጸ 35፣1-36፣7 አንብብ። ከሙሴን የአመራር ባሕርይ ያገኘውን ምላሽ መሠረት በማድረግ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚከተሉት ግምቶች ሊኖሩን ይችላሉ። እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ከትክክለኛው ጥቅስ ጋር አዛምድ። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘኸው ከአንድ የበለጡ ጥቅሶች መጠቀም ትችላለህ።

| ግምቶች | ጥቅሶች |
|---|---|
| ---------ሀ/ ሰዎች ግልጽ መመሪያ ይፈልጋሉ | 1/ 35፣10 |
| ---------ለ/ ሰዎች ግልጽ ግብ ይፈልጋሉ | 2/ 36፣2 |
| -------ሐ/ ብዙ ሰዎች ለመሥራት ፈቃደኛ ናቸው | 3/ 35፣21 |
| --------መ/ ብዙ ሰዎች ለመስጠት ፈቃደኛ ናቸው | 4/ 35፣35 |
| ------- ሠ/ ሰዎች ሞያን መማር ይችላሉ | 5/ 35፣1-3 |
| ----- ረ/ ሰዎች ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ዕውቀትና ችሎታ አላቸው | 6/ 35፣34 |

ብዙ ስለ አመራር ጥናት ያደረጉ ምሑራን እንደሚያምኑት ሰዎች በችሎታቸው እንደተጠቀሙበት ከተረዱ በተሻለ ሁኔታ ይሠራሉ። ዋጋ እንዳለው የሚያምኑበትን ነገር እንዲሠሩ ቢነገራቸው ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ለሥራው ይሰጣሉ። ስለ ሠሩትም ሥራ ምሥጋና ይፈልጋሉ።

የመገናኛው ድንኳን ሲሠራ ሙሴ የተጠቀመባቸው መመሪያዎች በጌታ ሥራም በጣም አስፈላጊ ነው። ሙሴ ለግለሰቦች እውቅና በመስጠት ስላላቸው ስጦታና ችሎታ በመመሪያ ደረጃ ክብሩን የሰጠው ለእግዚአብሔር ነበር። ይሁን እንጂ የዚያ ስጦታ፣ የሙያ እውቀትና ችሎታ ባለቤት የሆኑትን ሰዎች ስም በዝርዝር ያስታውቅ ነበር /ዘጸ 35፡30-35/

ይህን ውብና አስደናቂ ዓለም የፈጠረ እግዚአብሔር እጹብ ድንቅ የሆነ ልብስ ተክህኖ ለአሮን ከሰማይ ሊያወርድለት ይችል አልነበረምን? እግዚአብሔር ግን ያደረገው እንደዚያ አይደለም፡፡ አስፈላጊው ችሎታና ፈቃደኝነት ያላቸው ባለሙያዎችን ሙሴ እንዲመራና እንዲያስተባብር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ፡፡

እንግዲህ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎትና በሥራ ለመተርጎም ያላቸውን ፈቃደኝነት የምንገነዘብ ከሆነ፣ የመሪው ዋነኛ ሥራ ምን መሆን እንዳለበት መረዳት አያዳግተንም፡፡ የመሪው ሥራ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም ባላቸው ሞያ እንዲጠቀሙ እነዚህን ሰዎች ማቀናጀት ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለውም በሰዎች ችሎታ እምነት ሲኖረንና እነርሱን ወደ ጌታ የማምጣቱን እውነተኛ የሆነ ፍላጎት ሲኖረን ነው፡፡

11/ ለምሳሌ ያህል ማሕበረሰቡን የመንፈሳዊ ሥነ-ጽሑፍ ዘመቻ እንድትመራ ብትመረጥና መሪ ብትሆን ለዚሁም ሥራ የሚረዱህ ክርስቲያኖች ፍላጎቱ እንዳላቸውና ለመሥራትም ፈቃደኛ መሆናቸውን ካረጋገጥህ በኂላ ከሚከተሉት የትኛውን ታደርጋለህ?

ሀ/ ለእግዚአብሄር ሥራ ራስን የመስጠትን አስፈላጊነት መስበክ

ለ/ ሥራው መንፈሳዊ ግቦችን ለመምታት የታለመ መሆኑን መግለጽ

ሐ/ ለአገልግሎት በሚወጡበት ጊዜ ሌላ ሥራቸውን ሁሉ እርግፍ አድርገው እንዲተውት ማድረግ

መ/ አንዳንድ ሥራዎችን መስጠትና ጥያቄ እንዲያቀርቡ ጊዜ መስጠት

ረ/ አሁን ደግሞ ለምን እነዚህን እንደመረጥህ በሌላ ወረቀት ላይ ምክንያቶችህን አስፍር፡፡

በመሪነት ከተለያዩ ቡድኖች ጋር ሆነን ስንሰራ ግለሰቦች በሕብረት ሆነው ሲሰሩ የሚኖራቸውን ብርታት፣ችሎታና መንፈሳዊ ኃይል እንመለከታለን፡፡ ይህም የደስታችን ምክንያት ይሆናል፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶችን ሁኔታዎች የማያመቻቹ ሰዎች ግን ችግር ይጋብዛል፣ ሥራቸው አይሳካም፣ ክርስቲያናዊ ግቦችም ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

ከሙሴ ምሳሌነት እንደተረዳነው የእግዚአብሔር ሕዝብ የእርሱም ሕዝብ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ በዚህም ምክንያት በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ያላቸውን ችሎታና ኃይል እንዲያዳብሩ ሊረዳቸው ቻለ፡፡ ይህም መንፈሳዊ አመራር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡ ሰው ከሰው ጋር ለሚኖረው ግንኙነት አራት መመሪያዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መመሪያዎች በሥራ ላይ ከዋሉ ለአንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ችግር መፍትሔ ሊያስገኙ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

1/ ስለ ሁኔታው ያለህን ሃሳብ ወይም ስሜት ሰዎች በግልጽ እንዲያውቁልህ አድርግ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መሪዎች የቡድኑን ድካም የሚናገሩት ሌሎች እንጂ ለራሳቸው ሥራው ለሚመለከታቸው ወገኖች አይደለም፡፡

2/ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በመወያየት እርስ በርስ እንዲረዳዱ አድርግ

3/ የተለያዩ ሃሳቦችን እንዲያቀርቡና የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙበት ዕድል ስጣቸው፡፡ ይህን የሚያደርጉ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መምረጥና ኃላፊነትን ወስደው እንዲሠሩ ለማድረግ ይረዳል፡፡

4/ ስላከናወኑት መልካም ተግባር ለሰዎች አድናቆትህን ግለጽላቸው፡ ለእነርሱ ያለህን ቅን አመለካከትም እንዲረዱ አድርግ፡፡

12/ ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎች የማይከተል መንፈሳዊ መሪ ቢያጋጥምህና አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮችን እንድትለግሰው ቢጠይቅህ ምን ሃሳብ እንደምትሰጠው በዝርዝር አስፍር፡፡_______________________________________________

**የሙከራ ፈተና**

ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሻለ መልስ ነው ብለህ የምታስበውን ፊደል በመክበብ አመልከት፡፡

1/ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ዓላማ ስለነበረው ሙሴን ለመሪነት ጠራው፣ በድንቆችና በተአምራት መልክ ሥልጣንን ሰጠው፡፡ ከዚህም ሌላ፡-

ሀ/ በሕይወት ዘመኑና በዘላለም ሕይወቱ እንደሚሸልመው ተስፋ ሰጠው

ለ/ ከጠላቶቹ ጥቃትና ከወዳጆቹም ነቀፋ እንደሚጠብቀው ተስፋ ሰጠው

ሐ/ በሥራው ታዋቂ እንደሚሆንና እንደሚከበር ተስፋ ሰጠው

መ/ አብሮት እንደሚሆንና ታላቁን ዓላማውን እንደሚፈጽም ተስፋ ሰጠው

2/ እንደ ብዙዎቹ መሪዎች ሁሉ ሙሴ ስለ ሰዎች የሚያስብ ቢሆንም ከሚከተሉት በአንዱ ግን ይህን አይደለም የምንመለከተው፡

ሀ/ ስለሰዎች ደንታ ነበረው ለ/ ሕዝቡ ስላሉበት ሁኔታ ያስብና እነርሱን ለመርዳት አንድ ነገር ማድረግ ይፈልግ ነበር፡፡

ለ/ በጣም ትሁት ስለነበር የጌታን ጥሪ መቀበል አልፈለገም

ሐ/ በሕዝቡ ላይ የሚደረገውን ግፍ ለማስቆም ቆርጦ ተነሳ

3/ ከግብጽ የመውጣቱ ፍልሰት ሲጀመር አንድ የምንመለከተው ሰብዓዊ ባሕርይ አለ፡፡ አዲስ እንቅስቃሴ ሲጀመር ሰዎች በስሜት ይነሳሉ፣ መሪውንም ይከተሉታል፡፡ ውለው አድረው ችግሮች ሲመጡ ግን፡-

ሀ/ ስሜታቸው ይቀዘቅዛል፣ በረባ ባልረባውም መሪውን ይወቅሱታል

ለ/ ከዓላማቸው ይዘናጋሉ ሐ/ አመራሩ በአስቸኳይ እንዲለወጥ ይፈልጋሉ

መ/ ዓላማና ግባቸውን በአዲስ መልክ መገምገም ይጀምራሉ

4/ ውሃ ወደሌለበት ሥፍራ ሲደርሱ ሙሴ በጣም ተቸገረ፣ በዚህ ወቅት ከሙሴ ሕይወት የምንመለከተው ልምምድ ወይም ተሞክሮ ሌላ የመሪነት መመሪያ ያሳየናል፡፡ የአገልግሎት ልምምዶች ሸክም፡-

ሀ/ ሰዎችን ላዲስ ራዕይ ለማነሳሳት አስደናቂ ተአምራትን ይጠይቃል

ለ/ ከሌሎች መሪዎች ጋር የምንከፋፈለው ጉዳይ ነው

ሐ/ መሪው ብቻውን በርትቶ ቢጸልይ ሸክሙ ይቃለልለታል፡፡

መ/ አልፎ አልፎ ከረጅም ጊዜ ግቦቻችን ማረፍና አሁን ባለንበት ልምምድ ብቻ መርካት አለብን፡፡

5/ በረፋዲም ጦርነት የመሪነት መመሪያ ይገኛል፣ እግዚአብሔር ሙሴን፣

ሀ/ የጦርነቱን ታክቲክና የተደረገውን ቅስቀሳ በጽሑፍ እንዲያሰፍር ነገረው፡፡

ለ/ ወደ ውጊያው ስለሚሔዱ መካከለኛ መሪዎችና መሪውን ስለሚረዱት ተከታዮቹ በጽሑፍ እንዲያሰፍር ነገረው፡፡

ሐ/ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሰፈር ሊኖር ስለሚገባ ሞራል ነገረው፡፡

መ/ ለጦሩ ስለሚያስፈልገው ዝግጅትና የጌታን ውጊያ ለመዋጋት ስላላቸው ፈቃደኝነት በጽሁፍ እንዲያሰፍር ነገረው፡፡

6/ ሙሴ ስለ መሪነት ሌላ ትምህርት መማር ነበረበት፡፡ መሪነት፡-

ሀ/ ተገቢውን ሥራ ባይፈጽሙም እንኳ ሰዎችን መቀበልን ይጠይቃል

ለ/ በሕዝቡ መካከል ያለውን ቸልተኝነት በዝምታ ማለፍን ይጠይቃል

ሐ/ ቀድሞ ከነበረው ያነሰ ግብን ማስቀመጥ ያስፈልጋል

መ/ ራዕይ ለማካፈልና የታቀደውን ግብ እንዲመታ በሌሎች መታመን፡-

7/ ዮቶር ስለመሪነት ምክር ለሙሴ ሰጥቶት ነበር፡፡ ምክሮቹን በተግባር ቢያውላቸውን የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች እንደሚሆኑ ነግሮታል፡፡

ሀ/ ሰዎቹ ታማኝ ይሆናሉ፣ የታቀደውም ግብ ይሳካል፡፡

ለ/ ሥራው ይቃለልለታል፣ ሰዎቹም ይደሰታሉ

ሐ/ ሙሴ በሕይወት ይኖራል፣ የሕዝቡም ፍላጎት ይሟላል

መ/ ሙሴን የሚተኩ ወጣት መሪዎችን ማፍራት ይቻላል፣ ሙሴም ለዘለቄታው ታላቅ ሆኖ ይኖራል፡፡

8/ ሙሴን ታላቅ መሪ ካደረጉት ነገሮች አንዱ፡-

ሀ/ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማየት መቻሉ

ለ/ ቀድሞ ከነበረው ይልቅ ይበልጥ ለማከናወን የነበረው ራዕይ

ሐ/ ነገሮችን እውነቱ ባለበት ሁኔታ ይመለከታል እንጂ ሃሳባዊ አለመሆኑ

መ/ ከሕዝቡ ሁኔታ ጋር ለመጣጣም ከእነርሱ ዝቅ ያለ ነገርን መጠበቁ

9/ ሙሴ ሕጉን ለመቀበል ወደሲና ተራራ ወጥቶ በነበረበት ጊዜ ሕዝቡ ኃጢአት አደረጉ፣ እግዚአብሔር ሙሴን ***"ሕዝብህ"*** አለው፣ ሙሴ ደግሞ እግዚአብሔርን ***"ሕዝብህ"*** አለው፡፡ ስለ መሪነት ከዚህ የምናገኘው መመሪያ ምንድነው?

ሀ/ ሕዝቡ የእግዚአብሔር እንደመሆናቸው መጠን ተገቢውን ጥንቃቄ እንደሚያደረግላቸው መሪዎች በእግዚአብሔር መታመን እንዳለባቸው

ለ/ እግዚአብሔር ሕዝቡን በኃላፊነት ለመሪዎች ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር መታመንና ኃላፊነቱን መቀበል አለባቸው፡፡

ሐ/ ሥራው የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ እንደመሆኑ መጠን መሪዎች ይህን ያህል አገልግሎት ሊከብድባቸው አይገባም

መ/ በመሠረቱ መንፈሳዊ ሥራ እግዚአብሔርና ሰው በኃላፊነት የሚወጡት ሥራ ነው፡፡

10/ ዮቶር የሰጣቸውን ምክሮች በአጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል

ሀ/ "በመጀመሪያ ሕግ አውጣ ከዚያ በኋላ እንዲሰሩ ለሕዝቡ ንገራቸው፡"

ለ/ "ሕዝቡ ያለምንም ማወላወል እንዲታዘዙ ንገራቸው"

ሐ/ "ጽኑ ሥነ-ሥርዓት አስተምራቸው፡፡ ያጓደሉትን ግን ቅጣቸው"

መ/ በሕዝቡ ውስጥ ያልተጠቀመበት እምቅ ችሎታ አለ፣ ይህን ችሎታቸውን ሥራ ላይ እንዲያውሉት አድርግ።

11/ አንድ ሰባኪ "ለአንዳንድ የግል ጉዳዮቻችሁ ያለአግባብ የምትጠቀሙበትን ገንዘብ ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች ለማዳረስ እንዲቻል መስጠት አለባችሁ!" የሚል ከሆነ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር ሌሎችን ሁሉ ማለቱ ነው።

ሀ/ ሰዎቹ ራስ ወዳድ ስለሆኑ ገንዘባቸውን ለግላቸው ብቻ ያውሉታል

ለ/ መስዋእትነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ሌሎችን ወደጌታ ማምጣት አይፈልጉም

ሐ/ በተፈጥሮአቸው መልካምና እምነት የሚጣልባቸው ናቸው

መ/ ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ ወንጌል ላልደረሳቸው ማዳረስ ይቻል ነበር።

12/ ሰባኪው ሕዝቡ በጌታ ሥራ መሳተፍ ደስ እንደሚላቸው፣ ስላለባቸውም ኃላፊነት ለመማር ፈቃደኛ መሆናቸው በዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን ዓላማ እንደሚፈጸም ፍላጎት እንዳላቸው ቢገልጽላቸው ኖሮ ለሕዝቡ ያለው ግምት ምን ዓይነት እንደሆነ ነበር የሚያመለክተው?

ሀ/ ዝቅተኛ ግምት እንዳለው ለ/ ከፍተኛ ግምት እንዳለው

ሐ/ መጠነኛ ግምት እንዳለው መ/ ምንም ግምት እንደሌለው

13-14/ ከሚከተሉት ምሳሌዎች የትኛው ዓይነት የአመራር ስልት እንደተንጸባረቀ ከተመለከትክ በኋላ ይህ ዓይነቱ የአመራር ስልት በመሪውና በሕዝቡ ላይ የሚኖረውን የረጅም ጊዜ ተጽእኖ የራስህን አስተያየት ስጥ።

13/ አንደኛው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሰዎች ሁሉ ሰነፎች መሆናቸውንና በቅርበት ሊቆጣጠሯቸው እንደሚገባ ያምናል። ጥሩ ሲሰሩ ያመሰግናቸዋል፣ ጥሩ ካልሰሩ ግን ቅሬታውን ይገልጽላቸዋል። ሁሉንም ግብና እቅድ የሚያወጣው ራሱ ነው። ዝርዝር መመሪያ ይሰጣል ተግባራዊነቱንም በቅርብ ሆኖ ይከታተላል። ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው ይህን የአመራር ስልት በተሻለ ሁኔታ የሚገልጸው?

ሀ/ ስልቱ ብዙሐንን እንደሚያሳትፍ

ለ/ የሚከተለው በሥልጣን የተሞላ የአመራር ስልት እንደሆነ

ሐ/ በአንድ ሰው የተማከለ የአመራር ስልትን

14/ ሌላው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ደግሞ ደከመኝን የማያውቅ ሠራተኛ ነው። እንደ እርሱ ሌሎችም የሚያምኑበትንና ራሳቸውን የሰጡበትን ሥራ መሥራት እንደሚፈልጉም ያምናል። በሕዝቡ ውስጥ ያለውን ገና ያልተጠቀመብትን ችሎታና

ኃይል ያያል። አስፈላጊውን መመሪያ ያወጣል፣ ውሳኔ በመስጠቱ ላይ ግን ሁሉንም ያሳትፋል። የእያንዳንዱን ሰው ችሎታና ክህሎት በማዳበር ያምናል። አስተያየት እንዲሰጡና አስተዋጽኦ እንዲያደርጉም ዕድል ይሰጣቸዋል። ስለ መልካም ሥራቸው በሕዝብ ፊት ነው የሚያመሰግናቸው። የትኛውን ዓይነት አመራር ስልት ነው የሚከተለው?

ሀ/ ብዙሐኑን የማያሳትፍ የአመራር ስልት

ለ/ ሰዎች ኃላፊነት እንዲቀበሉ የሚያደርግ የአመራር ስልት

ሐ/ በአንድ ሰው ዙሪያ ያተኮረ የአመራር ስልትን

መ/ ብዙኃኑን የሚያሳትፍ የአመራር ስልትን

**አጭር መልስ**

ትክክለኛውን በባዶው ስፍራ በማስፈር ያልተሟላ ዐ/ነገሩን የተሟላ አድርግ።

- በአንድ ሰው ላይ ያተኮረ አመራር - ብዙኃንን ያቀፈ አመራር
- ገደብ የሌለው ሥልጣን ያዘለ አመራር

15/ አንድ መሪ ብቻውን አስፈላጊዎቹን ውሳኔዎች ሲያደርግ፣ ብቻውን ዝርዝር መመሪያ ሲሰጥና ቁጥጥር ሲያደርግ------------- አመራር ስልት ይባላል፡

16/ በቡድኑ ውስጥ ሆኖ የሚሰራ፣ ውሳኔና ሀሳብ በመስጠት የሚያሳትፍ ለሰዎችም ኃላፊነትን የሚያካፍል-------- አመራር ስልት ይባላል።

17/ ሰዎች ሁሉ ሰነፎች እንደሆኑና ለሥራ ማንቀሳቀስ እንዳለበት የሚያምን የሚከተለው የአመራር ስልት ------------ ነው።

18/ ስለ አመራር የጻፉ ብዙ ምሁራን እንደሚሉት ሰዎች በተሻለ መንገድ ለመሥራት ፈቃደኛ የሚሆኑት የተሰጣቸውን ስራ በሚገባ ማከናወናቸው ለዚህም ----------- ካገኙ ነው።

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

7 /ለ/ መዳበር የሚገባው ችሎታ እንዳላቸው ያውቃል።

ሐ/ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ያውቃል

መ/ እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዲከብር ይፈልጋል

1/ ሀ/ ሐሰት እግዚአብሔር ሳይጠራው በፊት እንኳ ሙሴ ስለሰዎች ያስባል

ለ/ እውነት ሐ/ ሐሰት አብሮት እንደሚሆን እንጂ እግዚአብሔር ሌላ ተስፋ አልሰጠውም መ/ እውነት ሠ/ እውነት ረ/ እውነት

8/ ሐ/ እንደሚገባ ከተረዱት ብዙ ሰዎች ሕግን ለማክበር ፈቃደኛ ናቸው

መ/ ብዙ ሰዎች የአመራር ችሎታ አላቸው

ሠ/ ተገቢውን ውሳኔ እንደሚያደርጉ በአብዛኛዎቹ ሰዎች መታመን

2/ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፣ አማረሩ ተነጫነጩ

9/ በአንድ ሰው ላይ ያተኮረ ዓይነት አመራር አስተያየት ነው ያለው

3/ አንዳንድ ሸማግሌዎችን ይዞ መሄድ ነበረበት

10/ሀ/5/35/፡1-3 ለ/1/35፡10 ሐ/2/36-32 መ/3/35፡21 ሠ/6/35፡34 ረ/4/35፣35

4/ ካለፈው ምንባብ መልስህን አስተካክል

11/ የተሻሉት ምርጫዎች "ለ" "መ" ና "ሠ" ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ሕዝቡ ወደ ስብሰባው የመጡት የጌታን ሥራ ለመሥራት ነው የሚል ሀሳብ ካለህ

ሀ/ አስፈላጊ አይደለም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስብከት የምታደርግ ከሆነ ሰዎችን እንዳልተረዳሃቸውና እንደማታደንቃቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ የአሁኑ ግብ ለዘላቂው ትምህርትና የሕይወት ዓላማ መሠረት ስለሆነ፡፡ የአሁኑ ግብ ለዘላቂው ትምህርትና የሕይወት ዓላማ መሠረት ስለሆነ፡፡ ለ/ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመንፈሳዊ አመራርም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመ/ እና በረ/ የተሰጡት መልሶች በሰዎች ላይ ያለንን አመኔታ ያሳያሉ፡፡

12/ መልስህ ከዚህኛው በመጠኑ ሊለያይ ይችላል፡፡ ቀጥሎ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች ተሰጥተዋል፡-

1/ የሚረዳህን ምረጥ ተገቢውን ሥልጠና ስጠው፡

2/ ለእያንዳንዱ ሰው የግሉን ሥራ ስጥ

3/ በወቅቱና በቅደም ተከተሉ መሰረት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ እያንዳንዱ የማለዳ ጸሎት እንዲኖረው አድርግ፡፡

4/ ተገቢውን ስልጠና ከሰጠህ በኃላ የክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፍ የሚሆን ሰው አስቀምጥ፡፡

5/ እያንዳንዱ ሰው የድርሻውን እንዲወጣ ኃላፊነት ስጠው

6/ ፕሮግራሙን ለማሻሻል ውይይት እንዲያደርጉ ለስብሰባ ጥራቸው፡፡

7/ ለቤተክርስቲያኑ እድገትና ለነፍሳት ወደጌታ መምጣት እያንዳንዱ ሰው ያረገውን አስተዋጽኦ አሳያቸው

6/ ሌሎች ሰዎች ሸክሙን ስለሚካፈሉ